የህግ የበላይነት

በዚህ አጭር ግንዛቤ የመስጫ ሰነድ ስለ የህግ የበላይነት ምንነት እና ለሀገራችን እና ለዜጎች ያለው ትርጉምና ከዚህ አንፃር ዜጎች ከሀገራቸው ምን እንደሚጠብቁ ወይም መብት እንዳላቸውና ከእነሱ የሚጠበቀውን ግዴታቸውን በመዳሰስ ግንዛቤ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

የህግ የበላይነት በጣም ሰፊና በርካታ መርሆችን ያቀፈ ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በአጭሩ እና ቀለል ባለ አገላለፅ የህግ የበላይነት ማለት በህግ መሠረት መግዛት እና መተዳደር ማለት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ በርካታ ጉዳዮች ይኖራሉ፡፡ በህግ መሰረት መገዛት ሲባል በምን አይነት ህግ የሚለው የመጀመሪያ ጥያቄ ነው፡፡ ህግ ማለት በአንድ ሀገር የሚኖሩ ሰዎች መብትና ጥቅማቸው የሚራገጥበት አስገዳጅ በሁሉም ሊከበርና ሊፈፀም የሚገባ ስርአት ሲሆን ከህጎች ሁሉ የበላይ ከሆነው ህገ መንግስት ጀምሮ አዋጆችን፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ ህጎች የሚወጡት በአንድ ሀገር ባሉ ህዝቦች ፈቃድና ስምምነት መሰረት በቀጥታና በተወካዮቻቸው አማካኝነት በሚወስኑትና በሚደነግጉት መሰረት የሚወጣ ነው፡፡ በተጨማሪም ህጎቹ መሰረታዊ የህግ መርሆችን እና ሀገሪቷ የተቀበለቻቸውን አለማቀፍ አስገዳጅ ለሰው ልጆች የሚገቡ ሰብአዊ መብቶችን በተከተለ መንገድ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ እነዚህ ህጎች የህዝቡን እና በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ግንኙነቶችን የሚመለከቱ አጠቃላይ ጉዳዮችን የሚገዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ስርአተ መንግስትን፣ የመንግስት አስተዳደር ሁኔታን፣ ህዝቡ ራሱን በራሱ እና በተወካዮቹ አማካኝነት እንዴት እንደሚገዛ፣ እንደሚተዳደር፣ የምርጫ ስርአቱን፣ መብቶቹን፣ መብቶቹ የሚጥሱ ሰዎችም እንዴት በወንጀል እንደሚጠየቁ፣ ውሎች በምን መልኩ እንደሚገቡና እንደሚከበሩ፣ የንግድ ስርአቱ እንዴት እንደሚመራ፣ የቤተሰብና ጋብቻ ስርአት እንዴት እንደሚጠበቅ፣ ውዘተ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የህግ የበላይነት ስንል በህግ መሰረት መገዛት ወይም መተዳደር ነው የሚለውን ካየን በኋላ ማን ባወጣው ህግ ነው የምንተዳደረው የሚለው ጥያቄ መታተየት አለበት፡፡ የአንድ ሀገር ህዝብ የሚተዳደረው በተስማማበትና ራሱ በራሱ ሊሆነ ይገባል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ የአንድ ሀገር ህዝብ ሁሉም በአንድ ጊዜ እነዚህን ዝርዝር የአስተዳደር ህግጋት ላይ ለመስማማትም ሆነ ለማውጣት ስለማይችል ተወካዮችን መርጦ በተወካዮቹ አማካኝነት እና በዴሞክራሲያዊ መንገድ አብዛኛው በሚስማማበትና በተቻለ መጠን በክርክርና በድርድር

በምክር ቤትና በጉባኤ መክሮና ዘክሮ ሁሉም የሚያማክል ህግ ይወጣል፡፡ በዚህ መልኩ በሚወጡ ህጎች የአንድ ሀገር ህዝቦች ይተዳደራሉ፡፡ በየደረጃው ያሉ ደንቦችና መመሪያዎችም በተመሳሳይ መልኩ በህዝብ ተወካዮች በሚሰጥ ፈቃድና ውክልና ወይም ስልጣን መሰረት በተቋማትና በአስፈፃሚዎች ይወጣል፡፡

የህግን ምንነት እና ህጉን ማን ያወጣዋል የሚለውን ጉዳዮች ካየን በኋላ የሚነሳው ጥያቄ ህጉን ማን ተግባራዊ ያደርገዋል እንዲሁም በህጉ መሰረት ዜጎችና ህዝቦች እየተዳደሩ መሆኑን ማን ያረጋግጣል ወይም በአፅድሩ ማን በህጉ መሰረት ያስተዳድራል የሚለው ነጥብ መታየት አለበት፡፡ የህግ የበላይነት ሲባል የግለሰብ ወይም የንጉስ ወይም የሆነ ቡድን አስተዳደር ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም የህዝብ አስተዳደር ማለት ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ህዝቡ የተስማማበት ወይም በተወካዮቹ አማካኝነት ባወጣው ህግ መሰረት አስተዳደር እንዴት እንደሚመረጥ፣ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚያስተዳድር፣ እንዴት እንደሚያስተዳድር፣ ስልጣኑ ምን እንደሆነ፣ ሀላፊነቱ ምን እንደሆነ በተደነገገው መሰረት የሚመራ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የህግ የበላይነት የሚረጋገጠው በህግ መሰረት በሚመረጥ የህዝብ ወኪል በመሆነ አስተዳደር በወጠለት ህግ መሰረት ሲያስተዳድር የህግ የበላይነት ተረጋገጠ ለማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ መሰረታዊና ቀለል ባለ መልኩ ከቀረበው አጠቃላይ ሀሳብ በማስከተል በህግ ይዘት ውስጥ፣ በህግ አወጣጥ ሂደት እና በህጉ አተገባበር ወይም አፈፃፀም ረገድ ስላለ የህግ መርሆች እንደሚከተለው በአጭሩ ይገለፃል፡፡

ህዝብ የሚተዳደርበት ህግ የበላይ የሆነው እና የበለጠ የሰፊው ህዝብ ተሳትፎና ቅቡልነት ያለው ህገ መንግስት የበላይነት መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ አንድም በህገ መንግስቱ ባራሱ የህጎች ሁሉ የበላይ መሆኑ በማወጅና በተግባርም እርሱን የሚጣረሱ ሌሎች ህጎችና አፈፃፀሞች ወይም ተግባራት ውድቅ እንዲሆኑ የሚደረግበት ስርአት መኖር ይህን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ለሰብአዊ መብቶች ከፍ ባለ ደረጃ በህግ እውቅና መሰጠቱ እና ተጥሰው ሲገኙም መፍትሄ የሚሰጥበት ስርአት እና የዚህም ውጤታማ አፈፃፀም መኖር የህግ የበላይነት መኖር ማሳያ ነው፡፡ በተመሳሳይ እኩልነት እና ፍትሀዊነት ለህግ የበለይነት መኖር አስፈላጊ መርሆች ናቸው፡፡ ህግ ለሁሉም በእኩል የሚየገለግል መሆኑ እና ሁሉም ከህግ በታች መሆኑ ብሎም ህጉ በሁሉም ላይ በእኩል ሲፈፀም የህግ የበላይነት

መኖሩን ያመለክታል። ህጉ በሚፈፀምበት ወቅትም በፍትሀዊነት እና ሰብአዊነት በተላበሰ መልኩ በርትእ በመተሳሰብና በወንድማማችነት ሲፈፀም የበለጠ ፍትሀዊ ይሆናል።

በሌላ በኩል የህዝብ ተሳትፎ የሚረጋገጥበት የዴሞክራሲ ስርአት ማለትም የምርጫና የህዝብ በመንግስት አስተዳደር የሚኖረው ተሳትፎ የተረገጋጠና የተከበረ መሆኑ ሌላው ማሳያ ነው። የመንግስት አስተዳደርም በግልፅነትና ህዝብን በማሳተፍ መከወኑ በአንፃሩም ስህተትና ጥፋት ሲያጋጥምም የተጠያቂነት ስርአት መኖሩ ስርአቱ የተደላደለና የዘፈቀደ አለመሆኑ ተቋማዊ መሆኑን ጥሩ ማሳያ ይሆናል።

ይህን ተጠያቂነት ለማጠናከርም ስልጣን በአንድ አካል ላይ እንዳይከማች የመንግስት ስልጣንን የሚከፋፍል የህግ ስርአት መዘርጋቱ የህግ የበላይነትን የበለጠ ለማረጋገጥ ያግዛል። የተከማቸ ስልጣን ለቁጥጥርና ተጠያቂነት አመቺ ባለመሆኑ አስተዳደሩ በህግ አውጪ፣ አስፈፃሚና ተርጓሚ ወይም ዳኝነት አካላት መከፋፈሉ አንዱ የሰራውን ሌላው ለመከታተልና ለማረም እድል በመስጠት የተጠናከረ የህግ የበላይነትን ያሰፍናል። ከዚህ አንፃር ሌላው በህግ የበላይነት ውስጥ ተግባራ ሆኖ ሊታይ የሚገባው መርህ የዳኝነት ነፃነት ነው። የዳኝነት አካሉ ከአስፈፃሚው ውጭ ሆኖ ዜጎች ከመንግስትም ሆነ ከሌሎች ግለሰቦች በደል ወይም የመብት መጓደል ሲደርስባቸው ጥያቄያቸውን አቀርበው መፍትሄ የሚያገኙበትን ዋስትና የሚሰጥ ይሆናል። በመጨረሻም ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚነሳው መርህ የመሰማት መብት ወይም (ዲዩ ፕሮሰስ) ስርአት ሊኖር ይገባል። በህግ መሰረት የዜጎችን መብትና ጥቅም የሚነካ እርምጃ ወይም ውሳኔ ሊወሰድ ሲል የሚመለከታቸውን ሰዎች የማስታወቅ ቅሬታም ካላቸው እንዲያቀርቡ እና በፍትሀዊነት ውሳኔ የሚሰጥበት ስርአት መኖሩ የህግ የበላይነትን የሚያረጋግጥ ይሆናል።

በአጠቃላይ የህግ የበላይነት ለመልካም አስተዳደር፣ ለእድገት እና ለሰላም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ትልቅ እሴት ነው። ለህግ የበላይነት መረጋገጥ ደግሞ ከላይ እንደተመለከተው እያንዳንዱ ዜጋም ሆነ የመንግስት አካልና ተቋማት ትልቅ ድርሻና ሀላፊነት እነዳለባቸው በግልፅ የሚያመለክት ነው። ይህም ሲባል መንግስት እና ሀላፊዎች በህግ መሰረት ብቻ በግልፅነትና ህዝብን በማሳተፍ ስራቸውን ማከናወን፣ ህግ አውጪዎች ምክንያታዊና ፍትሀዊ ህጎችን እንዲሁም የተሟሉ የህግ ስርአቶችን መዘርጋት፣ የዳኝነት አካሉ የዜጎችን የመሰማት መብት ጠብቆ በነፃነት ፍትሀዊ ውሳኔዎችን መስጠት፣ ዜጎች

ደግሞ አንዱ የሌላውን በህግ የተሰጠ መብት ማክበር፣ በመንግስት አስተዳደር ተሳትፎ ማድረግ፣ ጥያቄዎችን እና መብትን በህግ ስርአት መሰረት ማስፈፀምይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ዜጎች እና የህዝብ አገልጋዮች ይህን ሰፊ የህግ የበላይነት ማእቀፍ መረዳትና መብትና ግዴታን ማወቅ ለህግ የበላይነት መስፈን እና መረጋገጥ እንዲሁም መጠናከር አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡

የህግ ተግገርነት

ህግ የግለሰብ፣ ቡድን እና የህዝብን መብት፣ ጥቅምና ደህንነት ለማስጠበቅ እንዲሁም ያራ አስተዳደሩን ሁኔታ ለመወሰን ታልሞ የሚወጣ መሳሪያ ነው። ህግ እና ስርአት በሌለበት ግልሰብና ማህበረሰብ መብትና ጥቅሙን ለማስከበር አደጋች ከመሆኑም በላይ ጉልበት ያለው ፍላጎቱን ለማሳካት የሌላውን መብትና ጥቅም የሚወስድበት ስርአት የሌለበት ሁኔታ ይፈጥራል። በመሆኑም ህግ ስርአትን በማምጣትና የግለሰቦችን ብሎም የህብረተሰቡን ወይም የሁሉንም መብትና ጥቅም በሚያስከብር ሁኔታ ስርአት ለማበጀት የሚጠቅም ነው። ይህን ህግና ስርአት ለማስጠበቅና ለመቆጣጠር መንግስት ይደራጃል። ከዚህ አንፃር የህግና የመንግስት አስፈላጊነት ጉልህ መሆኑ ይታመናል።

መንግስት የሚደራጀው በአንድ ማህበረሰብ ወይም ህዝብ ወይም ሀገር ውስጥ ያሉ ግለሰቦችና ህዝቦችን መብትና ጥቅም ለማስከበርና ህግን ለማስፈፀም በማለም ነው። አሁን በደረሰንበት የእድገት ደረጃ መንግስት ከህዝቡ መሀል የሚውጣጣ የህዝቡ ውክልና ወይም ይሁንታን ያገኘ አካል ሆኖ የሚዋቀር ነው። መንግስት ህዝብ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር እንዲችል ከህዝቡ ውስጥ ሁሉም እኩል የመምረጥም ሆነ የመመረጥ እድል አግኝቶ ይህን የህብረተሰብ አገልግሎት ለመስጠትና ለማስፈፀም የሚደራጅ ነው። ሆኖም በአይነ ህሊናችን ህግና መንግስት የሌለበት አንድ ማህበረሰብን ለማሰብ ብንሞክር ይህ ህብተሰብ በምን መልኩ ሊተዳደርና የእለት ተእለት ኑሮውን ሊገፋ እንደሚችል ለማሰብ ቢሞክር በመጣም አስከፊ እንደሚሆን እሙን ነው። አንድ ግለሰብ ሁሉንም የሚያስፈልጉትን ነገሮች በራሱ ሊያሟላ ስለማይችል ምግቡን ለመሸመት፣ መጠለያ ለመስራት፣ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ፣ ስራ ሰርቶ ገቢ ለማግኘት እንዲሁም በደህንነት ለመኖር ህግና ስርአት የግድ ያስፈልዋል። አሊያ ጉልበት ያለው ያበቀለውን ሊወስድበት፣ የቀየሰውን መጠለያ ሊነጠቅ፣ በአገለልጋይነት በጉልበት ሊያዝ ይችላል። ስለሆነም የሰው ልጅ በታሪካዊ ሂደቱ ከገጠሙት ይህን መሰል ችግሮች ለመውጣትና አስተዳደሩን ለማዘመን ደረጃ በደረጃ በሂደት የአስተዳደሩን ሁኔታ በብዙ ድካምና ጥረት አሁን ከደረስንበት ዘመናዊ ዴሞክራሲያዊና ህገመንግስታዊ የአስተዳደር ደረጃ ላይ ደርሰናል።

ከዚህ ቀጥለን የህግን እና የመንግስትን ምንነት በአጭሩ ለማየት እንሞክራለን፡፡ ህግ ማለት በአንድ ሀገር የሚኖሩ ሰዎች መብትና ጥቅማቸው የሚራገጥበት አስገዳጅ በሁሉም ሊከበርና ሊፈፀም የሚገባ ስርአት ሲሆን ከህጎች ሁሉ የበላይ ከሆነው ህገ መንግስት ጀምሮ አዋጆችን፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ ህጎች የሚወጡት በአንድ ሀገር ባለ ህዝቦች ፈቃድና ስምምነት መሰረት በቀጥታና በተወካዮቻቸው አማካኝነት በሚወስኑትና በሚደነግጉት መሰረት የሚወጣ ነው፡፡ በተጨማሪም ህጎቹ መሰረታዊ የህግ መርሆችን እና ሀገሪቷ የተቀበለቻቸውን አለማቀፍ አስገዳጅ ለሰው ልጆች የሚገቡ ሰብአዊ መብቶችን በተከተለ መንገድ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ እነዚህ ህጎች የህዝቡን እና በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ግንኙነቶችን የሚመለከቱ አጠቃላይ ጉዳዮችን የሚገዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ስርአተ መንግስትን፣ የመንግስት አስተዳደር ሁኔታን፣ ህዝቡ ራሱን በራሱ እና በተወካዮቹ አማካኝነት እንዴት እንደሚገዛ፣ እንደሚተዳደር፣ የምርጫ ስርአቱን፣ መብቶቹን፣ መብቶቹ የሚጥሱ ሰዎችም እንዴት በወንጀል እንደሚጠየቁ፣ ውሎች በምን መልኩ እንደሚገቡና እንደሚከበሩ፣ የንግድ ስርአቱ እንዴት እንደሚመራ፣ የቤተሰብና ጋብቻ ስርአት እንዴት እንደሚጠበቅ፣ ወዘተ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ህጉን ማን ያወጣዋል ወይም ህዝብ የሚተዳደረው ማን ባወጣው ህግ ነው የሚለው ጥያቄ መታተየት አለበት፡፡ የአንድ ሀገር ህዝብ የሚተዳደረው በተስማማበትና ራሱ በራሱ ሊሆነ ይገባል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ የአንድ ሀገር ህዝብ ሁሉም በአንድ ጊዜ እነዚህን ዝርዝር የአስተዳደር ህግጋት ላይ ለመስማማትም ሆነ ለማውጣት ስለማይችል ተወካዮችን መርጦ በተወካዮቹ አማካኝነት እና በዴሞክራሲያዊ መንገድ አብዛኛው በሚስማማበትና በተቻለ መጠን በክርክርና በድርድር በምክር ቤትና በጉባኤ መክሮና ዘክሮ ሁሉም የሚያማክል ህግ ይወጣል፡፡ በዚህ መልኩ በሚወጡ ህጎች የአንድ ሀገር ህዝቦች ይተዳደራሉ፡፡ በየደረጃው ያሉ ደንቦችና መመሪያዎችም በተመሳሳይ መልኩ በህዝብ ተወካዮች በሚሰጥ ፈቃድና ውክልና ወይም ስልጣን መሰረት በተቋማትና በአስፈፃሚዎች ይወጣሉ፡፡

የህግን ምንነት እና ህጉን ማን ያወጣዋል የሚለውን ጉዳዮች ካየን በኋላ የሚነሳው ጥያቄ ህጉን ማን ተግባራዊ ያደርገዋል እንዲሁም በህጉ መሰረት ዜጎችና ህዝቦች እየተዳደሩ መሆኑን ማን ያረጋግጣል ወይም በአጭሩ ማን በህጉ መሰረት ያስተዳድራል የሚለው ነጥብ ይሆናል፡፡ አስተዳዳሪ ወይም መንግስት የሚሆነው ህዝቡ የተስማማበት ወይም በተወካዮቹ አማካኝነት ባወጣው ህግ መሰረት አስተዳደሪ እንዴት እንደሚመረጥ፣ ለምን ያህል ጊዜ

እንደሚያስተዳድር፣ እንዴት እንደሚያስተዳድር፣ ስልጣኑ ምን እንደሆነ፣ ሀላፊነቱ ምን እንደሆነ በተደነገገው መሰረት የሚመራ ነው።።

ከዚህ መሰረታዊና ቀለል ባለ መልኩ ከቀረበው አጠቃላይ ሀሳብ በማስከተል በህግ ይዘት ውስጥ፣ በህግ አወጣጥ ሂደት እና በመንግስት ህጉ ሲተገበር ወይም ሲፈፀም ሊጠበቁ ስለሚገባ የህግ መርሆች እንደሚከተለው በአጭሩ ይገለፃል።።

ህዝብ የሚተዳደርበት ህግ የበላይ የሆነው እና የበለጠ የሰፊው ህዝብ ተሳትፎና ቅቡልነት ያለው ህገ መንግስት የበላይነት መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል።። አንድም በህገ መንግስቱ ባራሱ የህጎች ሁሉ የበላይ መሆኑ በማወጅና በተግባርም እርሱን የሚጣረሱ ሌሎች ህጎችና አፈፃፀሞች ወይም ተግባራት ውድቅ እንዲሆኑ የሚደረግበት ስርአት መኖር ይህን ያረጋግጣል።። ከዚህ በተጓዳኝ ለሰብአዊ መብቶች ከፍ ባለ ደረጃ በህግ እውቅና መሰጠቱ እና ተጥሰው ሲገኙም መፍትሄ የሚሰጥበት ስርአት እና የዚህም ውጤታማ አፈፃፀም መኖር የህግ የበላይነት መኖር ማሳያ ነው።። በተመሳሳይ እኩልነት እና ፍትሀዊነት ለህግ የበለይነት መኖር አስፈላጊ መርሆች ናቸው።። ህግ ለሁሉም በእኩል የሚየገለግል መሆኑ እና ሁሉም ከህግ በታች መሆኑ ብሎም ህጉ በሁሉም ላይ በእኩል ሲፈፀም የህግ የበላይነት መኖሩን ያመለክታል።። ህጉ በሚፈፀምበት ወቅትም በፍትሀዊነት እና ሰብአዊነት በተላበሰ መልኩ በርትእ በመተሳሰብና በወንድማማችነት ሲፈፀም የበለጠ ፍትሀዊ ይሆናል።።

በሌላ በኩል የህዝብ ተሳትፎ የሚረጋገጥበት የዴሞክራሲ ስርአት ማለትም የምርጫና የህዝብ በመንግስት አስተዳደር የሚኖረው ተሳትፎ የተረገጋጠና የተከበረ መሆኑ ሌላው ማሳያ ነው።። የመንግስት አስተዳደርም በግልፅነትና ህዝብን በማሳተፍ መከወኑ በአንፃሩም ስህተትና ጥፋት ሲያጋጥምም የተጠያቂነት ስርአት መኖሩ ስርአቱ የተደላደለና የዘፈቀደ አለመሆኑ ተቋማዊ መሆኑን ጥሩ ማሳያ ይሆናል።።

ይህን ተጠያቂነት ለማጠናከርም ስልጣን በአንድ አካል ላይ እንዳይከማች የመንግስት ስልጣንን የሚከፋፍል የህግ ስርአት መዘርጋቱ የህግ የበላይነትን የበለጠ ለማረጋገጥ ያግዛል።። የተከማቸ ስልጣን ለቁጥጥርና ተጠያቂነት አመቺ ባለመሆኑ አስተዳደሩ በህግ አውጪ፣ አስፈፃሚና ተርጓሚ ወይም ዳኝነት አካላት መከፋፈሉ አንዱ የሰራውን ሌላው ለመከታተልና ለማረም እድል በመስጠት የተጠናከረ የህግ የበላይነትን ያሰፍናል።። ከዚህ

አንፃር ሌላው በህግ የበላይነት ውስጥ ተግባራ ሆኖ ሊታይ የሚገባው መርህ የዳኝነት ነፃነት ነው፡፡ የዳኝነት አካለ ከአስፈፃሚው ውጭ ሆኖ ዜጎች ከመንግስትም ሆነ ከሌሎች ግለሰቦች በደል ወይም የመብት መጓደል ሲደርስባቸው ጥያቄያቸውን አቀርበው መፍትሄ የሚያገኙበትን ዋስትና የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚነሳው መርህ የመሰማት መብት ወይም (ዲዩ ፕሮሰስ) ስርአት ሊኖር ይገባል፡፡ በህግ መሰረት የዜጎችን መብትና ጥቅም የሚነካ እርምጃ ወይም ውሳኔ ሊወሰድ ሲል የሚመለከታቸውን ሰዎች የማስታወቅ ቅሬታም ካላቸው እንዲያቀርቡ እና በፍትሀዊነት ውሳኔ የሚሰጥበት ስርአት መኖሩ የህግ የበላይነትን የሚያረጋግጥ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ የህግ የበላይነት ለመልካም አስተዳደር፣ ለእድገት እና ለሰላም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ትልቅ እሴት ነው፡፡ ለህግ የበላይነት መረጋገጥ ደግሞ ከላይ እንደተመለከተው እያንዳንዱ ዜጋም ሆነ የመንግስት አካልና ተቋማት ትልቅ ድርሻና ሀላፊነት እነዳለባቸው በግልፅ የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም ሲባል መንግስት እና ሀላፊዎች በህግ መሰረት ብቻ በግልፅነትና ህዝብን በማሳተፍ ስራቸውን ማከናወን፣ ህግ አውጪዎች ምክንያታዊና ፍትሀዊ ህጎችን እንዲሁም የተሟሉ የህግ ስርአቶችን መዘርጋት፣ የዳኝነት አካለ የዜጎችን የመሰማት መብት ጠብቆ በነፃነት ፍትሀዊ ውሳኔዎችን መስጠት፣ ዜጎች ደግሞ አንዱ የሌላውን በህግ የተሰጠ መብት ማክበር፣ በመንግስት አስተዳደር ተሳትፎ ማድረግ፣ ጥያቄዎችን እና መብትን በህግ ስርአት መሰረት ማስፈፀምይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ዜጎች እና የህዝብ አገልጋዮች ይህን ሰፊ የህግ የበላይነት ማእቀፍ መረዳትና መብትና ግዴታን ማወቅ ለህግ የበላይነት መስፈን እና መረጋገጥ እንዲሁም መጠናከር አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡

ሀላፊነት

ህግ

የህግ አወጣጥ

የመንግስት አካላት - ዳኝነት

የሀገራችን አላማ ሰላም ልማት መልካም አስተዳደር/ዴሞክራሲ

የህገመንግስት የበላይነት

ሰብአዊ መብት

እኩልነት እና ፍትሀዊነት

ተሳትፎ፣ ግልፅነት፣ ተጠያቂነት

ስልጣን ክፍፍል

ዳኝነት ነፃነት

ዲዩ ፕሮሰስ

የዜግነት ግዴታ

ቤተሰብን ማክበር

ታላላቆችን ማክበር

የሀይማኖት መሪዎችን ማክበር

ለአረጋውያን ለአካል ጉዳተኞች ህፃናትና ሴቶች ቅድሚያና ክብር መስጠት

የሌሎችን መብት ማክበር

የሀሳብ ልዩነትን እና ብዝሀነትን ማክበር

ስራን/ሀላፊነትን ማክበር

ህግ አስከባሪን ማክበር

መንግስትን ማክበር

ህጎችና ደንቦችን ማክበር

ትራፊክ ደንብን መክበር

ማህበራዊ ሀላፊነትን መወጣት ቮለንቲሪዝም

አካበቢን አለመበከል